# የሰብዓዊ መብት ጥሰትና የዘር ማጥፋት ወንጀል በኢትዮጵያ:

## ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ በእንግሊዝ ፓርላማ ተካሄደ

ከንጉሤ ጋማ



**የሁሉም ፓርቲዎች የፓርላማ ቡድን በ3ኛዉ ዓለም ትብብር/ All Party Parliamentary Group on the Third World Solidarity/** በመባል የሚጠራዉ ድርጅት በታላቋ ብሪታኒያ ከሚገኙ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላት ጋር በመተባበር ያዘጋጀዉ እና በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ላይ የተወያየ ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ በለንደን ተካሄደ::

በምርጫ 97 የአዉሮፓን የምርጫ ታዛቢ ቡድን የመሩት የአዉሮፓ ህብረት የፓርላማ አባል የተከበሩ ወይዘሮ አና ጎሜዝ እና **የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የወዳጅነት ንቅናቄ /Solidarity Movement of New Ethiopia/ SMNE/** ዲሬክተርና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች አቶ ኦባንግ ሜቶ በክብር እንግድነት በተገኙበት በዚህ ስብሰባ ላይ የእንግሊዝ የፓርላማ አባላት፣ጥሪ የተደረገላቸዉ እንግዶች፣ የኦጋዴን ሶማሊያ ተወላጆች፣ የኢትዮጵያ ወዳጆች የሆኑ የተለያዩ አገራት ዜጎች እንዲሁም በርካታ ኢትዮጵያዊያን ተገኝተዋል::



በእንግሊዝ ፓርላማ ፖርትኩሊስ ሃዉስ Portcullis House የተደረገዉን ስብሰባ የመሩት የሁሉም ፓርቲዎች የፓርላማ ቡድን የ3ኛዉ ዓለም ትብብር ሊቀመንበር የሆኑት ካዉንስለር ሙሽታክ ላሺር ናቸዉ:: የኢትዮጵያዉ ማህበረሰብ አስተባባሪ አቶ ከፍያለዉ ማሞ የስብሰባዉን ዓላማ በሰፊዉ አስረድተዋል:: በመለስ ዜናዊ የሚመራዉ የወያኔ ኢሕአዴግ መንግስት ወደሥልጣን ከመጣበት ከ1991 እኤአ ጀምሮ በአገራችንና በሕዝባችን ላይ እያደረሰ ያለዉ ኢሰብዓዊ ተግባር እጅግ የሚዘገንን መሆኑን በመግለፅ በተለይም በምርጫ 97 ከፈፀመዉ ወንጀል በከፋ መልኩ መጪዉን የ2002 ምርጫ ዜጎችን በመግደል፣ በማሰርና በማንገላታት እንዲሁም በተለያየ ጥቅማ ጥቅም በመስጠት በሥልጣን ላይ ለመቆየት ከወዲሁ በማድረግ ላይ ያለዉ ሴራ በከፍተኛ ደረጃ አሳሳቢ መሆኑን አመላክተዋል::



በኢትዮጵያ በስልጣን ላይ ያለዉ አምባገነን ቡድን በሕዝብ ላይ በመፈፀም ላይ የሚገኘዉ ኢሰብዓዊ ተግባር በዩናይትድ ኪንግደም የሚገኘዉን በትዉልድ ኢትዮጵያዊ በዜግነት ብሪታኒያዊ የሆነዉን ሁሉ እጅግ እንደሚያሳስበዉ የገለፁት አስተባባሪ፣ የዩናይትድ ኪንግደም መንግስት የ1988 የወንጀለኛ ህግ አንቀፅ 134 እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ጉባዔ እኤአ በ1984 ባፀደቀዉ ደንብ መሰረት መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቻቸዉ በሕዝብና በአገር ላይ ለሚያደርሱት ወንጀል ለፍርድ የሚቀርቡበትን ሁኔታ እንዲፈጠር ጠይቀዋል፡፡ የዩናይትድ ኪንግደም መንግስት አምባገነን ከሆኑት ዘረኛ ወንጀለኞች ይልቅ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንዲቆምና በኢትዮጵያም ላይ የሚከተለዉን ፖሊሲ በጥልቀት እንዲመረምር ያሳሰቡት አስተባባሪ፣ በዩናይትድ ኪንግደም የሚገኘዉ ብሪታኒያዊ ኢትዮጵያዊ ወደፊት በማንኛዉም ጊዜ መለስ ዜናዊ ወደ ለንደን ቢመጡ የዜግነት መብቱን በመጠቀም እርምጃ ለመዉሰድ ዝግጁ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በቁጥር 200 የሚሆነዉን የአዉሮፓ ኅብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን በመምራት የወያኔ ኢህአዴግ መንግስት በአሳፋሪ ሁኔታ የተጋለጠበትን የግንቦት 1997 ዓም ምርጫ የታዘቡት የዕለቱ የክብር እንግዳ የተከበሩ ወ/ሮ አና ጎሜዝ ሂደቱን በምሬት በማስታወስ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ በወቅቱ መላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የስርዓት ለዉጥ ለማድረግ የነበረዉ ከፍተኛ ፍላጎት፣ ያሳየዉ በሳል የፓለቲካ አመለካከትና ጨዋነት ምን ጊዜም ሊዘነጋ እንደማይችል ጠቅሰዋል፡፡ በአምስት ዙር የተካሄደዉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምረጡኝ ቅስቀሳና ክርክር የወያኔ ኢሕአዴግ ፓርቲን ማንነት በእጅጉ ያጋለጠ እንደነበረ በማስታወስ የጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መንግስትና የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ እዉነታዉን ለማደባበስ፣ ለመደበቅና ለመቆጣጠር እንዳልቻሉ ገልፀዋል፡፡ ምርጫዉ በተካሄደበት ዕለት ገና ቆጠራዉ ሳይጠናቀቅ መንግስት ይወስዳቸዉ የነበሩት ሕገ ወጥ ተግባራት፣በመንግስት መገናኛ ብዙኃን ይሰጡ የነበሩት መግለጫዎች በጠቅላላዉ የምርጫዉን ዉጤት ተዓሚኒነት እንዳይኖረዉ ከማድረግ አልፎ ተርፎ በተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችና በንፁኃኑ ሕዝብ ላይ ሊደርስ የሚችለዉን ግድያ፣ እስራትና እንግልት በግልፅ ይጠቁም እንደነበር በዝርዝር አስረድተዋል፡፡ ድምፃቸዉ እንዲከበር በሠላማዊ መንገድ ጥያቄ ያቀረቡ ከ200 ያላነሱ ኢትዮጵያዊያን በመንግስት



የፀጥታ ኃይሎች በጥይት ግንባራቸዉን እየተመቱ ሲገደሉ፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩት ወደ ተለያዩ እስር ቤቶች ሲወረወሩ በስፍራዉ የነበሩት የተከበሩ ወ/ሮ አና ጎሜዝ አንድ የ13ዓመት ታዳጊ ወጣት ከመኖሪያ ቤቱ በመንግስት ወታደሮች ተጎትቶ ለእስር ሲዳረግ መመልከታቸዉን ከመግለፃቸዉም በላይ መረን የሆነዉ የመለስ ዜናዊ መንግስት በእሳቸዉና በቡድናቸዉ ላይ በመንግስት መገናኛዎች ያካሄደዉን የስም ማጥፋት ዘመቻ አስታዉሰዋል፡፡ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ የሚሰጣቸዉን የሀሰት መረጃዎች እንዲደግፉና ምርጫዉ ዲሞክራሲያዊ እንደሆነ ምስክርነታቸዉን እንዲሰጡ፣ ይህን ካልፈፀሙ ግን ደም መፋሰስና እርስ በርስ የመተላለቅ ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል፣ በአገሪቱ አንድነትና ሠላም ላይ ለተደቀነዉ አደጋ ኃላፊነት እንደሚወስዱ በግል ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ ቢደርሳቸዉም ይህንን ዓይን ያወጣ ተግባር በምንም መልኩ ሊቀበሉት እንዳልቻሉና እሳቸዉና ቡድናቸዉ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን መቆምን እንደመረጡ በስሜት ተናግረዋል፡፡

ወያኔ/ኢህአዴግ የሕዝብን ድምፅ ከመስረቅ አልፎ ተርፎ በተፈጠረዉ ግጭት ንፁኃን ዜጎችን ከመግደል ከማሰር እንዲሁም የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን፣ የነፃዉ ፕሬስ አባላትን፣የሲቪክ ማህበራት እና የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን በሀሰት ክስ ለእስር እንደዳረጋቸዉ፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዛሬም ወ/ት ብርቱኳን ሚደቅሳ ዳግመኛ የዕድሜ ልክ ተበይኖባት በእስር ላይ እንደምትገኝ አብራርተዋል፡፡ በጠ/ሚኒስትር መለስ የሚመራዉ የኢትዮጵያ መንግስት በሀሰትና በስርቆት የሚያምን አምባገነን በመሆኑ እኤአ በ1984 በተከሰተዉ የረሃብ አደጋ ከዓለም አቀፉ ህብረተሰብ በእነ ቦብ ጊልዶፍ ባንድ ኤይድ የተሰበሰበዉን የርዳታ እህል በመሸጥ ገንዘቡን ለጦር መሳሪያ መግዣ እንዳዋለዉ መስማታቸዉ እንዳላስገረማቸዉ የገለፁት የተከበሩ ወ/ሮ አና ጎሜዝ ከዚሁ ድርጊት ባልተናነሰ ሁኔታ ዛሬም የወያኔ መንግስት የአገሪቱን መሬትና ሕፃናት በመሸጥ ላይ እንደሚገኝ በቁጭት ገልፀዋል፡፡



መጪዉን የ2002 ምርጫ በተመለከተ በኢትዮጵያ በምንም ዓይነት ሁኔታ የጠ/ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መንግስት ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ያካሄዳል ብለዉ እንደማይገምቱ ያላቸዉን እምነት አልሸሸጉም፡፡ ምዕራባዊያን የጠ/ሚኒስትር መለስን መንግስት ማንነት በግልፅ የሚያዉቁት ይሁን እንጂ ለአገሮቻቸዉ ፍላጎት ከሚሰጡት

ቅድሚያና ከሚከተሉት ፖሊሲ አንፃር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመቆም ትርጉም ያለዉ ስራ መስራት እንደማይፈልጉ በመግለፅ ኢትዮጵያዊያን በዘርና በፖለቲካ አመለካከት በመካከላቸዉ ያለዉን ልዩነት በማስወገድ በጋራ ተነስተዉ የጋራ ችግራቸዉን ማስወገድ



እንደሚጠበቅባቸዉ አብራርተዋል። የአዉሮፓ ኅብረት የ2002 ምርጫን ለመታዘብ የሚያስችለዉን ሁኔታ በተመለከተ ዉሳኔ ላይ ያልደረሰ መሆኑን በመግለፅ፣ የምርጫዉ ዉጤት ምንም ይሁን ምን፣ የኢትዮጵያ መንግስት ሁሉንም ነገር በሚያመቸዉ መንገድ አድበስብሶ እንዳያስቀረዉ በስፍራዉ ተገኝቶ በመመልከት ሁኔታዉን ለሕዝብ ማሳወቅ አንድ አማራጭ ሲሆን በሌላም መልኩ ትርጉም የማይኖረዉን የይስሙላ ምርጫ መታዘብ ያለአግባብ ገንዘብና ጊዜን ማባከን ሊሆን እንደሚችል ግምት ዉስጥ በማስገባት የኅብረቱ መታዘብና ያለመታዘብ ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑን የተከበሩ ወ/ሮ አና ጎሜዝ አልሸሸጉም።

ሌላዉ የክብር እንግዳ አቶ ኦባንግ ሜቶ በበኩላቸዉ ምርጫ 97ን ተከትሎ በአገራችንና በሕዝባችን ላይ የደረሰዉን ግፍ በመግለፅ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ነፃና ገለልተኛ ባልሆነበት መልኩ፣ ከ95% በላይ የሆነዉ የአገሪቱ የመከላከያ ኃይል በአንድ ብሄረሰብ ቁጥጥር ስር በዋለበት፣ ነፃ ጋዜጦችና የዜና ማሰራጫዎች በሌሉበት እንዲሁም የፍትህ ተቋማት ሙሉ በሙሉ የወያኔ ኢህአዴግ አገልጋይ በሆኑበት ስርዓት ዉስጥ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ከቶዉንም ሊታሰብ እንደማይችል አብራርተዋል። ግልፅነትና ተጠ ያቂነት በሌለበት ሁኔታ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በኦጋዴን፣ በደቡብና በሌሎችም ክልሎች ዉስጥ በዜጎች ላይ ኢሰብዓዊ ግፍና በደል በመድረስ ላይ እንደሚገኝ የገለፁት አቶ ኡባንግ ሜቶ፣ አምባገነኑ ስርዓት የምርጫ ሥነ ምግባር ሰነድ በማዘጋጀት የሚያካሄደዉ መከባ "የአጥፍቶ ጠፊ አጋሮቼ" የሚላቸዉን ምዕራባዊያን መንግስታት ለማደናገር የሚጠቀመዉ ስልት መሆኑን ተናግረዋል። የዩናይትድ ስቴትስ፣ የእንግሊዝ፣ የካናዳ እና የሌሎችም ምዕራባዊ አገሮች መንግስታት ከራሳቸዉ ብሄራዊ ፍላጎት ባለፈ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተንሰራፋዉን አምባገነን ስርዓት ለማስወገድ ትርጉም ያለዉ ተሳትፎ እንደማይኖራቸዉ በመግለፅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነዚህ መንግስታት የሚያስተላልፈዉ መልዕክት ቢኖር **"በትግል ጎዳናችን ላይ እንቅፋት አትሁኑብን፣ የመለስን አምባገነን መንግስት በተለያየ መንገድ በመደገፍ የስልጣን ዕድሜዉን በማራዘም የነፃነት ጉዟችንን አታደናቅፉት"** የሚል ይሆናል ብለዋል።

የ3ኛዉ ዓለም ትብብር የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት ጋዜጠኛ ወ/ሮ ሳንድራ ሳተርሊ በበኩላቸዉ ባደረጉት ንግግር ኢትዮጵያ በዓለም በድህነት ከሚታወቁት አገራት በግንባር ቀደምነት እንደምትጠቀስና ካጠቃላይ ሕዝቧ ከግማሽ በላይ የሚሆነዉ ከድህነት ወለል በታች ባለዉ መስፈርት በረሃብና በችግር በመሰቃየት ላይ መኖሩን፣ ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ መንግስት በየወቅቱ በተወሰነ አኃዝ የኢኮኖሚ ዕድገት እንደሚያሳይ የሚያወጣቸዉ መግለጫዎች ከእዉነታዉ የተቃረኑ እንደሆነ አመልክተዋል። የአገሪቱ የሰብዓዊ መብት አጠባበቅ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሚገኝም ጠቅሰዋል።

እኤአ በ1960ዎቹ በለጋ የወጣትነት ዕድሜያቸዉ ኢትዮጵያን የሚያዉቋት መሆኑን የገለፁት ወ/ሮ ሳንድራ ኢትዮጵያ በዓለም ስልጣኔ ዉስጥ እጅግ የተከበረ ታሪካዊ ስፍራ እንዳላት፣ ሕዝቦችዋ የመከባበር ባህልና ጨዋነት ያላቸዉ እንደሆኑ በመግለፅ ዴሞክራሲ፣ ሠላምና ፍትህ የሰፈነበት ስርዓት ባለቤት እንዲሆኑ ከጎናቸዉ መቆም ይኖርብናል ብለዋል። ለዚህም መጪዉ ምርጫ ነፃና ፍትሃዊ እንዲሆን ጥረት ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበዋል።

በዚሁ ታላቅ ስብሰባ ላይ በመገኘት ሃሳባቸዉን ከገለፁት መካከል የፓርላማ አባላት፣ የኢትዮጵያ ወዳጅ እና የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ደጋፊ የሆኑ የዉጭ አገር ሰዎች፣ ጋዜጠ ኛና ደራሲ፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፣ አቶ አየለ አንጀሎ የቀድሞ የቅንጅት አመራር አባል እና ሌሎችም ግለሰቦች ይገኙባቸዋል።

በስብሰባዉ ላይ ሃሳባቸዉን የሰነዘሩት በሙሉ ***ኢትዮጵያዊያን ለመብታቸዉና ለነፃነታቸዉ ከራሳቸዉ በላይ ማንም ሊቆምላቸዉ፣ ሊታገልላቸዉና ሊሞትላቸዉ እንደማይችል ጠንቅቀዉ በመረዳት በመካከላቸዉ ሊፈጠሩ የሚችሉ ማናቸዉንም የጎሳና የፓለቲካ የአመለካከት ልዩነቶችን በማስወገድ በአምባገነኑ የመለስ ዜናዊ መንግስት ምትክ የሕዝባቸዉ ይሁንታና ፈቃደኛነት የሚኖረዉን ስርዓት ለመመስረት በጋራ በመቆም ወቅቱ የሚጠይቀዉን መስዋዕትነት ለመክፈል ቆርጠዉ መነሳት እንዳለባቸዉ አስገንዝበዋል።***



የዕለቱ ስብሰባ እንዳይካሄድ በመወትወት በዩናይትድ ኪንግደም የሚገኘዉ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ከ600በላይ ደብዳቤዎችን ለፓርላማ አባላት፣ መንግስታዊ ለሆኑና ላልሆኑ ድርጅቶች የበተነ ቢሆንም ስብሰባዉ በታቀደለት ቀንና መንገድ ያለ አንዳች እንከን መካሄዱ ያስደሰታቸዉ መሆኑን የ3ኛዉ ዓለም ትብብር ሊቀ መንበር ካዉንስለር ላሻሪ ለተሰብሳቢዉ ገልፀዋል። በማያያዝም በዩናይትድ ኪንግደም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዉስጥ የኢትዮጵያ ጉዳይ አንድ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ የሚቀርብበትን መንገድ በማመቻቸት ላይ መሆናቸዉን የገለፁት ሰብሳቢ ለዚሁ እንዲረዳ Early Day Motion በትዉልድ ኢትዮጵያዊያን



የሆኑ የብሪታኒያ ዜጎች የፓርላማ ተጠሪዎቻቸዉን በማግኘት ሰነዱን እንዲያስፈርሙ ጠይቀዋል። የስብሰባዉ ተካፋዮች በጠቅላላዉ በተለይም በስፍራዉ የተገኙት ኢትዮጵያዊያን ከአምስት ዓመታት በፊት በግንቦት 1997 የተካሄደዉን ምርጫ የአዉሮፓ ኅብረት ታዛቢ ቡድን ሰብሳቢ በመሆን በወያኔ ኢህአዴግ ማስፈራሪያና የስም ማጥፋት ዘመቻ ሳይበገሩ ለመላዉ ዓለም ላጋለጡት ለተከበሩ ወ/ሮ አና ጎሜዝ ያላቸዉን ከፍተኛ አክብሮት ገልፀዋል።

በግንቦት 97 የተደረገዉን ምርጫ ተከትሎ በኢትዮጵያዉ አምባገነን መሪ መለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትዕዛዝ ግምባራቸዉ በአግዓዚ አባላት ጥይት እየተመታ የተገደሉትን ንፁኃን ዜጎች የአሟሟት ሁኔታ የሚያሳዩ ፎቶዎች ተባዝተዉ በስብሰባዉ ላይ ተበትነዋል። በተከታታይ ለ3 ሰዓት የተካሄደዉ ስብሰባ ከምሽቱ 3:30 ተኩል ላይ ተጠናቋል።